EthioLion

# የስደቱ ወለፈን በኖርዌ

(ክፍል ሶስት)

ከብ.ወ

## ስደት የንዋይ ፍሰት፣ መብት፣ ወይንስ እንግልት?

የንጉሡ ዘመን ሰዎችና ስደት ብዙም አይተዋወቁም። ጥቂቱ - እጅግ ጥቂቱ - በሥርዓቱ ላይ ያመጹት ወይንም ንጉሡን ያንቋሸሹት ኬንያ፣ ሱዳን ወይም ባቅራብያው በሚገኘው አንድ የጎረቤት ሃገር ይሸሸጋሉ። በሀገር ቢኖሩም ኖሮ በግዞት ሊቀጡ የሚችሉ ጥፋተኞች ነበሩና በመሰደዳቸው ራሳቸውን ለባሰው ቅጣት እንደዳረጉ ተቆጥሮ ቸል ይባላሉ እንጂ "ፈልጋችሁ አምጧቸው" አይባልም። ሆኖም ግን በዚሁ በንጉሡ ዘመን ኢጣልያ አርባ አመት ሙሉ ተዘጋጅታበት የአድዋውን ሽንፈቷን በበቀል ልትወጣ እጅግ ብዙ ዘመናዊ ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖችን አስከትላ ሕጻኑን አዋቂውን በግፍ እየቆላች ወደ ውስጥ ስትገፋ - "ሀገሬ በጠላት እጅ ስትወድቅ አላይም" - ብሎ የተሰደደ ብዙ ነበር። ኃላ ግን አብርሃም ደቦጭና ሞገስ አስግዶም ግራዚያንን በቦንብ ሲያናውጡ፤ ዘርዓይ ደረስ በሮም አብዲሳ አጋ በኢጣልያ በርሃዎች ጀብዱ ሲፈጽሙ፤ እነ አበበ አረጋይ፣ ደስታ ዳምጠው፣ በላይ ዘለቀ፣ ሽመልስ ኃብቴ፣ ኃይለማርያም ማሞ፣ በቀለ ወያ፣ መስፍን ስለሺ፣ በየነ መርዕድ፣ ኃይሌ ሸንቁጥ - ወዘተ በዱር በጫካው ጠላትን አንቆራጠውና መድረሻ አሳጥተው ወደ መጣበት በውርደት ሲያባርሩት እነዚያ የተሰደዱት ሁሉ በሆታ ተመልሰዋል። ታድያ ባንዳ፣ ስደተኛና አርበኛ የተባለውም ክፍፍልም የመጣው ያኔ ነበር። ንጉሡ ባንዳውን ሲሾሙ "ሀገሬ ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ - የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ" - በማለት አዝማሪውም የወቅቱን ፖለቲካ ባጭር ስንኝ ቃኘው።

ከሚከተለው ርዕዮተ ዓለም አንጻር ሸቀጦችን፣ ፊልሞችንና ባህሉን በመገደብ የምዕራቡን ዓለም ብርቅዬ ያደረገው የደርግ አገዛዝ ነበር። ራምቦ፣ ዘ ቻምብና ዘ ካራቴ ኪድስ ፊልሞች የምዕራቡን ጉደኛ አለም ስበው እፒያሳ ድረስ አመጡት። ወዲህ ደግሞ እነማይክል ጃክሰን፣ ማዶና፣ ሊዮኔል ሪቼ፣ ዊትኒ ሃውስተንና ስቴቪ ዎንደር የመሳሰሉት ዝነኛ አቀንቃኞች በቪዲዮ ሲበተኑ ወጣቱ እንደጊዮርጊስና እመብርሃን ያመልክላቸው ጀመር። አምባገነኑ ደርግና ስደትን የቋመጠው ወጣት ሊደማመጡ አልቻሉም። ደርግ ብሄራዊ ውትድርና ሲል አኩብካቢው ወጣትም ከዚህ መዓት ይድን ዘንድ ለዋሺንግተኑኑ ሊበርቲ ሃውልትና ለፓሪሱ ታወር መስገዱን ጀመረ። ታድያ ፓስፖርት ማግኘት ቀርቶ የደርግን ኬላዎች ሰብሮ ማለፍ እንደ ጠፈር ጦርነት አስቸጋሪ ሆነ። ቪዛው ረክሶ ደብተሩ ከየት ይምጣ። እንደ እድል ሆኖ የቻለው በቦሌ ያልቻለው በባሌ እየወጣ አሜሪካና አውሮፓ ገብቶ የሚልካቸው ፎቶግራፎች፣ ቲ-ሸርትና ስኒከርስ ጫማ የየኔታ ገብረመስቀልን ልብ እንኳን ሳይቀር አሸፈተ። ደርግም ዋዛ አይደለም ለስደቱ ትልቅ ግንብ አበጅቶ አምባገነናዊ ውሳኔዎቹን ማጽናቱን ተያያዘው። ይህም ሆኖ በርካቶች ሳይሰደዱ ሀገራቸው በጽናት ሲያገለግሉ ቆይተዋል። በሌላ በኩልም ለትምህርት፣ ለሥራ፣ ለጉብኝትና ለሕክምና የሚወጣው ብዙ ሰው ጉዳዩን ጨርሶ ወደ ሃገሩ ይመለስ ነበር። ለምን እዚያው አልቀራችሁም? ተብለው ሲጠየቁ መልሳቸው - "ኢትዮጵያን ለደርግ ማን ሰጠው" - ነበር።

ወያኔ ለሀገር አንድነት ያለው ፍቅር የላላ በመሆኑ ለስደቱ ብዙ ግምት አልሰጠውም። እነዚያ ለስደት ቋምጠው የነበሩትን ወጣቶችና አንዳንድ ተማርን የሚሉ ዘመናዊነቱን ናፋቂ "ምሁራን" በነፍስ ደረሰላቸው።

EthioLion.Com

ደርግ የገነባውን ግድብ ጠርምሶ የስደቱን ጎርፍ ለቀቀው። "እረ ብዙ ተመራማሪዎችና የሕክምና ባለሙያዎች ሀገሪቱ እየለቀቁ ነው" - በማለት የሀገር ተቆርቋሪዎቹ ሲጮሁ - ወያኔ - "ስደትን ከመገደብ ይልቅ አባይን መገደብ ይቀላል" – በማለት አፌዘ። በወያኔ የአገዛዝ ዘመን ሕዝቡ እንዲሰደድ ያደረጉት ጉስቁልናዎቹና የሰብዓዊ መብት ረገጣዎቹ ናቸው። በእርግጥ እኚህ የተሰደዱት ለየቤተሰቦቻቸው የሕይወት መቆያዋን ባይልኩ ኖሮ የወቅቱ ዋጋ ግሽበትና የኑሮ ውድነቱ ብዙዎችን ያሰቃይ ነበር።

ሀገራቸውን የለቀቁ ወደ 215 ሚሊዮን የሚጠጉ ስደተኞች በዓለም ላይ አሉ ይባላል። እ/ኤ/አ በ 2011 ዓም ከለሙት ሀገሮች ወጥቶ ወደ አለሙት ሀገሮች የገባው ገንዘብ 372 ቢሊዮን ዶላር ነበር። ሕንዶች 58 ቢሊዩን ዶላር፣ ቻይኖች 57 ቢሊዮን ዶላር፣ ሜክሲካውያን 24 ቢሊዮን ዶላር፣ ፊሊፒንሶች 23 ሚሊዮን ዶላር ሲልኩ ፓኪስታኖች፣ ባንግላዲሾች፣ ናይጀርያውያን፣ ኔፓሎች፣ ቬትናሞች፣ ግብጻውያን፣ ሊባኖሶች በየፈርጁ በርካታ ገንዘቦችን ልከዋል።

ከ 620 000 በላይ እንደሆኑ የሚገመቱት ኢትዮጵያውያን ዲያስፖራዎች እ/ኤ/አ በ 2010 ዓም ወደ 387 ሚሊዮን ዶላር ወደ ሀገራቸው አፍሰዋል ይላል አንድ የአለም ባንክ መረጃ። በርካታ ኢትዮጵያውያን በሱዳን፣ አሜሪካ፣ እስራኤል፣ ጅቡቲ፣ ኬንያ፣ ሳውዲ፣ ካናዳ፣ ጀርመን፣ ጣልያን፣ ስዊድን ይኖራሉ። ከነዚህ ሀገሮች አንጻር ሲታይ ኖርዌ ብዙ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች የሏትም። ታድያ ጥንት ይፈሩና ይከበሩ የነበሩትን የጀግኖች ልጆች ሃገራችንን ልቀቁልን ማለቷ አስገርሟልም አሸማቋልም።

ከላይ እንደተመለከትነው ስደት እንደ ነዋይ መፍሰስ (remittance) ሊቆጠር ይችል ይሆናል። ሆኖም ግን ምዕራብያውኑ ሀገሮች ከሀገራቸው በፍሰት መልክ የሚወጣውን ገንዘባቸውን መመለስ የሚችሉ መለኞች መሆናቸውን መዘንጋት የለብንም። አንደኛው ስልታቸው አምባገነኑን ሥርዓት ለነሱ እንዲመች አድርገው መኮትኮት ነው። ታድያ ጥቂቱ ቱጃር ነጋዴና ባለስልጣኖች በዝርፊያና በሙስና ያካበቱትን ገንዘብ ወደ ውጭ ለሸርሽር፣ ለዘመናዊ ቤቶች መግዢያ፣ ለልጆቻቸው መማርያ፣ ለዘመናዊ ሕክምና፣ ወዘተ - ሲያወጡት ወዲህም ዘመናዊና ውድ ተሽከርካሪዎችን ባስገቡ ቁጥር የነዳጅ ፍጆታው ሲጨምር፣ ውድ ልብሶችን፣ ጫማዎችንና የቅንጦት እቃዎቹን ሲያስመጡ - ወዘተ - የውጭ ምንዛሬው ተዝቆ ሲወጣ ምዕራብያውያን ፍሰቱን ያቻችልላቸዋል። ደሀው ሕዝብ ደግሞ በኑሮ ውድነትና በዋጋ ግሽበት መከራውን ያያል።

የአለምአቀፉ ስደተኝነት ድንጋጌዎች ብዙ ናቸው እጅግ ብዙ። ሰዎች በመረጡት ቦታ የመኖር መብት በነዚሁ ደንቦች የታቀፈ - በሄልሲንኪ ኮንፈረንስ በበርሊን በሌሎችም የአውሮጳ መዲናዎች የተደነገጉ ናቸው። እያደርም የወጣው የ 1975 ዓም የስደተኛ ሠራተኞች ህግ - የ 1980 ዓም ለተረጂዎች የሕክምና አሰጣጥ ሕግ። የቪየና ኮንቬክሽን፣ የተባበሩት መንግስታት ድንጋጌዎች፣ የ UNHCR ደንቦች - እጅግ ብዙ ህጎች አሉ። የስደተኝነት ድንጋጌዎች መጻፍ የተጀመሩት በአንደኛውና በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት የአውሮፓ ሕዝቦች መውጫያ መግቢያ ባጡበት ጊዜ በሌሎች ሀገሮች እየሄዱ መጠለያ እንዲያገኙ ለማስቻል ነው። ብዙዎች ማንነታቸውን ሳያሳውቁ በፈረንሳይ በሃንጋሬ በቼክ ተጠልለዋል። የናዚ ወንጀለኞችም ሳይቀር በርካታ ገንዘቦችንና ወርቆችን ዘርፈው ወደ ላቲን አሜሪካ ሸሽተዋል። በእስራኤል ደህንነቶች እስኪያዙ ድረስ እዚያው ላቲን የተደበቁ ብዙዎች ሲሆኑ አንዳንዶቹም ሳይደረስባቸው ቀርተው

EthioLion.com

እዚያው ተቀብረዋል። አንዳንዶቹም ንሥሃ ከገቡ በኋላ በፈቃደኝነት ራሳቸውን ለሕግ ሲያቀርቡ ቆይተዋል።

የስደተኞች መብት ድንጋጌዎች የፈለቁት በእንዲህ ዓይነቱ መልክ ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት የሶቭየት ሳተላይት ከነበሩት እንደ ኢትዮጵያ፣ አንጎላና ኩባ ካሉ ሃገሮች ሰዎችን በማሰደድ የሶቪየቶችን አለም አቀፍ ጉልበት ለማድከም ምዕራብያኖች የተጠቀሙበት ልዩ ልዩ የስደት የድንጋጌ ታክቲኮች አሉ። ታድያ መቼውንም ቢሆን ምዕራብያኖች የአፍሪካን ደሃ ሕዝብ ለመጥቀም ድንጋጌዎች አያወጡም። እነዚህኑ ድንጋጌዎች መስበር ሲፈልጉ ኖርዌ ከኢትዮጵያ ጋር እንዳደረገችው ዓይነት ችግሮችን ተግባብቶ መፍታት የሚይስችል ግኑኝነቶችን ይሰራሉ (MoU – Memorandum of Understanding) ። ታድያ ስደት መብት ነው የሚለው አጠያያቂ ይሆናል። ዛሬ መብት መስሎ ቢታይም ነገ ደግሞ መብቱን የመግፈፍ ሥራ ሊከናወን ይችላል። ሕጎች በተለዋወጡ ቁጥርም ክብርን ማቆየት ይከብዳል (Difficult to Normalize the Status)። ስደትን የሚያበዙትም የሚቀንሱትም እነሱ ራሳቸው ፈረንጆቹ ናቸው። በእርግጥ ስደት እጅግ በርካታ የውጭ ምንዛሬን ከማስገኘቱ አኳያ ለደሃ አገሮች ጠቀሜታነቱ እንከን የለሽ ቢሆንም እንኳን አድካሚ ወይንም ቀላል ሥራ የተሰማራው ሠርቶ አደርም ሆነ ተሸከርካሪ ወንበር ላይ የተቀምጠው ምሁር - የሕይወቱ ውጣ ውረድና ባይተዋርነቱን ሳያብከነክነው አይቀርም። የወላጅ እናት ሀገሩ ጉስቁልና፣ እርዛቱና ረሃቡ በብዙሃን መገናኛዎቹ ሲለቀቁ አይቶ ማዘኑና ማፈሩም አይቀርም። ሌላው ቢቀር ጉልበቱንም አእምሮውንም ያጣችው እናት ሀገር በዲሞክራሲ ስም በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዙ ስትበዘበዝ የማይገደው ይኖር ይሆን?

ስደት ብዙ ያንገላታል። እንግልቱ የብሱን አቋርጦ ባህሩን ሰንጥቆ አንድ የታለመ ሀገር ከመድረስ ጀምሮ የተቀበለችዋ ሀገር መልስ እስክትሰጠው ድረስ ያለውን ዘመን መበሻቀጥን ያካትታል። ይህ የእንግልት ዘመን ከአንድ ወር እስከ ብዙ አመታት ሊፈጅ ይችላል ይሆናል። በነዚሁ ከአንድ ወር እስከ ብዙ ዓመታት ባለው ጊዜ በስደተኛው የውስጥ ስሜት መድቀቅ አንስቶ (Depression) -"ምነው እግሬን ባላነሳሁ" - እስከሚያስብለው ዓይነት የአዕምሮ ወቀሳ (Guilt) መጠበስ አለ። ፈቃድ የማግኘቱ ጉዳይ እጅግ ከረዘመም ይኸው የውስጥ ችግር ይባባሳል። ከእንግልቱ ባሻገር - በምኞት መቃጠሉና - በኑሮ መራወጡ በተጨማሪም - "አይ የኔ ነገር" - የሚያስብለው መብከንከን በእጅጉ ያንገሸግሻል። ከዛሬ ነገ አገሬ እመለሳለሁ የሚለው ባይተዋር - "በምን ይዤ ልግባ" - ሰቆቃ ሲዋዥቅ - ልቡ ለመመለስ የተነሳሳው ደግሞ የአምባገነን ሥርዓቱን ውድቀት ሲጠብቅ አልያም ምኞቱን ትቶ መውጣቱ አላስችል ብሎት - ልቆይ፣ ልቀመጥ፣ ልሂድ ሲል ዘልዛላ እድሜው ትገነሸራለች።

መብከንከኑ - ውስጡ - የውስጡ ምስጢር የገባው ላይ ይበዛል። አንድ ሰሞን ሲታታተም በነበረው የጦብያ መጽሄት (አምስተኛ ዓመት - ቁጥር ስምንት ገጽ 5 – 8 (14) ላይ አቶ ጸጋዬ ገብረ መድኅን አርአያ "የመንፈስ ስደተኝነትስ - የመንፈስ ድርቀትስ" - በሚለው አርዕስት ሥር ላይ ሲከትቡ "ስለስደተኞች መወያየት ግን ነገሩን ያሰፋውና ከአጉል አምባጓሮ ውስጥ ይከተናል። ምክንያቱም የውስጡ የውጪውን የሚያይበት፣ የውጭው የውስጡን የሚያይበት መነጽር "የእይታ ጥራት" ምን ጊዜም አስተማማኝ አይሆንም" ብለዋል። በመጣጥፋቸው መሃል ላይ ደግሞ "ይህ ሁሉ የባለታሪክ፣ የኩሩ ኢትዮጵያዊ ልጅና የልጅ ልጅ ስደተኛ መባሉ እንደ ሸማ እንደማይሞቀው እናውቃለን..." ሲሉ ሃቁን አስረድተዋል። በመጨረሻም "ታድያ ሁሉም የኢትዮጵያ ልጅ ወደ ስደት ሲጓዝ ተጉዞም በድል

የሚመለስበትን መንገድ ራሱ ሲያጥረው፣ በተጨማሪ በሺህ የሚቆጠሩ ውድ አእምሮዎች በሎተሪ ሲወሰዱብን ሁላችንም ከአገራችን ለአገራችን ሳንሆን ስንቀር ለነገ አመራር የሚውል ሰው አለን ይባላል? ስደት - የአካል ስደት፣ የአዕምሮ ስደት፣ የመንፈስ ስደት - መቼ ነው የሚያበቃው? ሲሉ ጽሁፋቸውን በጥያቄ ይቋጫሉ።

ለኢትዮጵያውያን - "ኢትዮጵያ የዓለሙ ሁሉ መፋረጃነቷ" - ለተገለጸላቸውና በታላላቅ የሃይማኖቱ መጽሃፍት የተጠቀሰችዋን ኢትዮጵያ ለተቀበሉት ደግሞ የውስጥ አበሳው ይበልጥ የሚርመሰመሰው ኢትዮጵያዊነቱን ራሱ ሰርዞ ዜግነቱን - "የወርቁን ስጦታ" – ከተቀበለ ዕለት ጀምሮ ነው። የቴዎድሮስን፣ የዮሐንስንና የሚኒሊክን ጥቁሩን ካባ አንስተው የነሱን ነጩን ካባ ሲደርቡለት የማይቆጭ ኢትዮጵያዊ ምናልባት ጥቂት ቢሆን ነው። ታድያ ነጮቹ ይህን ሲያደርጉ በጦርነት ያልተበገሩላቸውን እነዛን አንበሶች እንደተበቀሉት ይቆጥሩታል። ይሄ የውስጥ አበሳ ሁሉንም ላይነካ ይችላል። ለገባቸው - "አገር ማለት በመወለድ አትብት በመሞት አካል ከአፈሩ ጋር ስለሚዋሃድ የአገሩ አፈር ሕዝብ በለዩ የሚኖርባት ማለት ነው" - ተብሎ የክቡር ዶክተር ከበደ ሚካኤል ትምህርቶችን ለጤኑ፣ የባንዲራን ምስጢርና የአርበኝነትን ገድል ለሚያስታውሱ፣ ኢትዮጵያውነትን መለወጥ እያደር እንደ አባ ጨጓሬ እብደሚኮሰኩስ ያውቁታል። በእርግጥ ብዙዎች ዜግነቱን የለወጡት ለመጓጓዣነቱ ጥቅም እንጂ ሃገርን ከመክዳት አኳይ አይደለም ብለው የሚናገሩም አሉ።

ቤኔት (Bennett) የተባሉ አንድ ተመራማሪ በጻፉት ጥናታዊ ጽሁፍ ላይ "ለመሆን ብቻ ፈልገው" ዜግነት የተሰጣቸው (Actualizing Citizens) ከትክክለኛ ሃላፊነቱ ከሚሰማቸው ዜጎቹ (Dutiful Citizen) መካከል የሚታይ ልዩነት እንዳለ አስቀምጠዋል። ብዙዎች የወረቀት ዜጋዎቹ ለመንግስቱ ሥራ ፈጽሞ ደንታ የሌላቸው (Diminished Sense of Government Obligation) ከፍተኛ የግለኝነት ስሜት የተላበሱ (Higher Sense of Individual Purpose) ናቸው ይላሉ። ዜግነቱን ለሰጣቸው ሀገር የፖለቲካ ጉዳዮችና ምርጫዎች ላይ ከመሳተፍ ይልቅ ሸቀጦች በማየትና በመግዛት (Consumerism) ጊዜአቸውን የሚያጠፉ፣ በሀገሪቱ ፖለቲከኞችና የዜና ስርጭት ላይ አመኔታ የሌላቸው (Mistrust of Politicians and Media)፣ ከጥቂት መሰሎቻቸው ጋር ብቻ ህብረትን የፈጠሩ (Thin Social Ties)፣ እንዲሁም በስም በለው ኢንፎርሜሽን የሚነዱ ናቸው ይላል። አብዛኛውን ጊዜ ዜግነታቸውን የለወጡ ሰዎች ከሁለቱም ሀገሮች ባህልና አመለካከት ውጭ በመሃል የሚዋዥቁ ለግል ኑሯቸውና ምቾት ወይም በሀገራቸው ለሚገኙት ቅርብ ዘመዶቻቸው ብቻ የሚጨነቁ አናሳ የእድገት አስተሳሰብ ያላቸው ግለሰቦች ናቸው ይላል ጽሁፉ። ዞሮ ዞሮ ግን ይላሉ ጸሃፊው - አንድ ግለሰብ የትውልድ ሀገሩን ብሄራዊ ስሜት (Nationalism) ፈጽሞ ፍቆ ወረቀት ለሰጠው ሀገር እውነተኛ ተቆርቋሪ ዜጋ (Dutiful Citizen) ሊሆን እንደማይችል ያብራራሉ። ለምሳሌ አሜሪካዊ ዜግነቱን ያገኙት ሕንዶች በሃሳብና ተግባር ግን ለሕንድ ብሔረተኝነት ቅድሚያ ይሰጣሉ ሲሉ አያይዘው ይናገራሉ። በዚህም ሳብያ የሕንድ ዲያስፖራዎች ወደሀገራቸው ከፍተኛ ንዋይ ብቻ ሳይሆን ቴክኖሎጂንና ሳይንስን በማፍሰስ ረገድ እጅግ አመርቂ ሥራን እየተገበሩ ነው።

የስደቱ ወለፈን በኖርዌ ለጊዜው አረጭ ያለ ይመስለል። መልካም ክንውኖቹ ፖሊሲውን አንገጫግጨውታል። እግዚአብሄር ደግሞ ሥራውን ይሰራል። ለሰው የመይቻለው ሁሉ ለእግዚአብሄር ይቻላል። ከሩቅ ሆነን የምናያት ያች ሀገር - ያች አምሳለ ገነት - በጠላቶቿ ተቀነባብሮ ከሚሠራባት ሤራ

EthioLion.Com

ተላቃ ነገ ሁላችንንም ታሰባስባለች የምንለው በእግዚአብሄር ያለን እምነት የፀና ስለሆነ ነው።ይህ በኖርዌ ስደተኞች ላይ የደረሰው መከራ እሥራኤል ባሉት ላይም ሊተገበር የተዘጋጀ ይመስላል ። እስራኤል ውስጥ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ከቅርብ ጊዜህ ወዲህ በሀገሪቱ ላይ በመጣው የዘር አንግልት እየተጉላሉ ነው። ዜግነቱን ያገኙትም እንኳን ቢሆን ውጡ እንደተባሉት ሁሉ ባንድ መስፈርት ስለታዩ ፍርሃቱ በዝቶባቸዋል።

ወገኖቼ ስደት ምንድነው? የንዋይ ፍሰት፣ መብት፣ ወይንስ አንግልት? እስቲ እናንተም የራሳችሁን ፍርድ ሥጡ። ለሁሉም ግን በአዕምሮ መበልጸግ፣ ጥልቅና መንፈሳዊ ነገሮችን መረዳት መቻል ጠቃሚ ነው። ይህ ካልሆነ ደግሞ መሻሻል የለም።

የሆነው ሆኗል - ያለፈው አልፏል - የወደፊቱን ለማስተካከል መረባረቡ ላይ ነው ትልቁ ቁምነገር። የኢትዮጵያዊያኑን የስደት ጎርፍ መገደቡ ላይ ነው ተግባራችን መጉላት የሚያሻው። ለተሻለ ኑሮ ሲል የአውሬ እራት፣ የቀማኞች ሲሳይ፣ የግፈኞች ሰለባ የሆነውን ወገናችንን ተረባርበን ማዳን አለብን። እንዴት? - ልንነጋገርበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ኢትዮጵያ ለዜጎቿ ምቹ እንድትሆን ከመታገል በላይ የሚያስመካ ነገር የለም። መሰደድ ተምሮ ወይንም ገንዘብ ጨብጦ መመለስ ቢሆን ኖሮ እሰየው። መሰደድ ቀልጦ መቅረት ወይንም ላይኖሩበት ሀገር ቤት ጎጆ መቀለስ ብቻ ከሆነ ግን ከንቱ ነው። ከውጭ ያሉ የሀይማኖት፣ የፖለቲካና የኪነጥበቡ ሰዎች ለውጭ ድርጅቶቻቸው መጎልበት ሲሉ መሰሎቻቸው ሲሰደዱላቸው ደስ ይላቸው ይሆናል። ወያኔስ ቢሆን እነዚህ የሀገር እሴቶችና ፈርጦች ውልቅ ሲሉለት ምን ጎድሎበት። ወርቁን አንደሆነ ይዘው አይወጡ። በዚህም በዚያም ተጎጂዋ እናት ሀገር ብቻ ነች።

ሌላው ተልኳችን የወያኔውንና የምዕራቡን አለም "የእከክልኝ ልከክልህ" ዲፕሎማሲያዊ ግኑኝነት ለማስቀም በጥበብ መታገሉ ነው። በዲፕሎማሲውና በአለም አቀፉ ግኑኝነት ሙያና ልምዱ ያለቸው ሁሉ ለዚህ በጎ ተግባር ራሳቸውን ማነሳሳት ይገባቸዋል።

በውጭ የምንገኝ ሁሉ ልጆቻችንን የኢትዮጵያን ባህሉንና ቋንቋውን ማስተማሩን አኩሪ ታሪካችንን ማስጨበጡ ደግሞ ሌላው ግዴታችን ነው። ይህ በጎ ክንውን በምዕራቡ ሀገሮች ይታያል። የኢትዮጵያ ማህበሮች በዚህ ጉዳይ ላይ ትልቅ ትኩረት ሰጥተው በሚታይ ተግባር መንቀሳቀሳቸው ሊያስመሰግናቸው ይገባል። ዛሬ በስደት አብረውን የሚገኙት ልጆቻችን የነገው ውድ ሀገራችን ተረካቢዎች መሆናቸው አይቀርም። እነዚህ በአስተሳሰብ የታነጹትና በመልካም ባህርይ የበለጸጉት ልጆች የሀገር ቤቱን ሥርዓት ሲረከቡ ሙስናው ቀንሶ ዲሞክራሲው ይበዛል - ቴክኖሎጂና የስነ ፍጥረት ምርምሩ ወደ ሀገራችን ፈሶ ረሀብና እርዛቱ ታሪክ ይሆናሉ።

እግዚአብሄር ይመልከተን ወደ ተግባርም ያንደርድረን። ሞክረን ያቃተንን ብቻ ለሱ እንተወዋለን። የተሰደዱት ሁሉ መልሳቸውን አግኝተው ልባቸው ታርፍ ዘንድ እግዚአብሄር አፋጣኝ መልስ እንዲሰጥ እንጸልያለን። ያልተሰደዱት ደግሞ ረግተውና ጸንተው በሀገር ይቆዩ ዘንድ እግዚአብሄር ምቹ ሁኔታን እንዲፈጥርልን እንጸልያለን። አሜን

bisrat.smart@yahoo.com